# ሃሳቦች በዛሬዉ የለዉጥ ትግል - ሥርዓት ለዋጭ እንቅስቃሴዎች እንዴት

( ክፍል አንድ)

ተስፋዬ ደምመላሽ

April 24, 2017

በረጅሙ የአብዮትም የድህረ አብዮትም ዘመን ኢትዮጵያ ህልዉናዋን ተፈታታኝ ለሆኑ ተደራራቢ ፖለቲካ ወለድ ዉጥረቶች የተጋለጠች አገር ናት። እስከ ዛሬ ድረስ ራሷን ያቆየችዉ ካፈራቻቸዉ የተማሩ ሰዎችና ፖለቲከኛ አድራጊ ፈጣሪዎች ምንም ያህል የብሔራዊ ሕይወት ጥበቃ እገዛ ሳታገኝ ብቻ አይደለም። ላለፉት አራት አስርተ አመታት ቀጣይ ሆና መቆየት የቻለችዉ በታሪካዊ የዝግመት ሃይሏ የአብዮተኛ ምሁራንን፣ ፖለቲከኞችንና አገዛዞችን የትም የማይወስዱ “ተራማጅ” ሃሳቦችና እንቅስቃሴዎች በመቋቋምም ነዉ።

ዛሬ በሕወሓት አገዛዝ ሥር እርግጥ ከመቸዉም ጊዜ ይበልጥ አስከፊ የሆነ የመከፋፈል ጥቁር ደመና አገሪቱ ላይ እያንዣበበ ነዉ። ይህም ሁኔታ ቢያንስ በከፊል የአብዮቱ ዘመን ተረፈ ዉጤት መሆኑ ስዉር አይደለም። ኢትዮጵያ ከዉስጧ በፈለቀ የአገር ዉቃቢ የራቀዉ አብዮታዊ ተብዬ መሰሪ የ“ብሔሮች” እና “ህዝቦች” ፖለቲካ ተመትራ፣ ተቀንሳና አንሳ በከባድ የሞት ወይም የሽረት ዉጥረት ተይዛለች። በጨለማ ዘመን ዉስጥ ትገኛለች። ነገር ግን የተጓደለና በዘር ወገነተኝነት የተጨናነቀም ቢሆን አንድነቷ አሁንም አለ፤ ህልዉናዋ አካቶ አልጠፋም። ዛሬ ቢመሽና ቢጨልምም ለኢትዮጵያ በሩህ ነገ አለ። ይህ ዝምብሎ ምኞታዊ እሳቤ ሳይሆን አሳማኝ ምክንያቶች ላይ የተመሠረተ ተስፋ ነዉ። ከታሪክ እንደምንማረዉ ኢትዮጵያዊነት ከዉስጥም ሆነ ከዉጭ የሚሰነዘርበትን በደልና ተጕጂነት ጸጥ ብሎ ተቀባይ ሆኖ አይቀርም። ወይም ደግሞ ዝምብሎ የምሁራንን እና የፖለቲከኞችን መታደግ አይጠብቅም። ዉሎ አድሮም ቢሆን ራሱ ተነሳሽና ተንቀሳቃሽ ሃይል ነዉ፤ የማንሰራራት፣ መልሶ የመጠናከርና በትግል ጠላቶቹን ተቋቁሞ የማሸነፍ ባህልና ልምድ አለዉ። ነገደ ብዙዉ የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪክ፣ በተለይ በቀዉጢ ጊዜያት ደጋግሞ እንዳሳየዉ በተባበረ አልሞት ባይ ተጋዳይነት የጋራ ብሔራዊ ሕይወቱን ከጥፋት አዳኝ ነዉ። ስለሆነም በዘረኞች የተነጠቀዉን አገሩን መልሶ መዉሰድ የሚያስችለዉ እምቅ አቅም አለዉ። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ዛሬ ከምትገኝበት ወድቀት መነሳት የምትችለዉ የአንድነቷ እድሳት፣ ጥንክርና ቀጣይነት በተደራጅ እዉን ጥረት ሲረጋገጥ እንደሆነ እንረዳለን። ምሁራዊ ግጥሚያና አመራር የዚህ ሁለገብ ጥረት ዋና አካል መሆኑንም እንገነዘባለን። ግን በአገር አድን ትግሉ ፈላጭ ቆራጩን የሕወሓት አገዛዝ በሃሳቦች መስከ መቋቋም ምን ፋይዳ አለዉ?

በሌላ አባባል፣ የወያኔ አገዛዝ በቀና አገራዊ መንፈስ ሊሳተፍበት በማይፈልግ ወይም በማይችል ነፃ የሃሳባና የፖለቲካ ዉድድር ተቃዋሚ ወገኖች አገዛዙን ለምንና እንዴት መግጠም ያስፈልጋቸዋል? ገዢዉ ፓርቲ ሊቀበላቸዉ ቀርቶ በሃቀኝነት ሊያስተናግዳቸዉ ፈጽሞ በማይሻ ጽንሰሃሳባዊና መርሃዊ ፈርጆች ዙሪያ እንዴት ተብሎ ነዉ ከፓርቲዉ ጋር “መደራደር” ወይም መታገል የሚቻለዉ? ፓርቲዉ ከተቃዋሚ ወገኖችና ምሁራን ጋር በተንኮል ሳይሆን በግልጽነትና በበጐ እምነት የሃሳቦች ልዉዉጥ ዉስጥ ይገባል ተብሎ የሚጠበቅ መሆኑ ይቅርና የሚታሰብስ ነዉ ወይ? ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ በቀጥታም ሆነ በጨረፍታ አስተዋጽዎ የሚሆን ዉይይት በዚህ ጽሑፍና በተከታዩ (ክፍል ሁለት) ከማቅረቤ በፊት ከአገር አድን ትግሉ አኳያ “ምሁር” እና “ምሁራዊ ሥራ” የሚሉትን ቃላት ባጭር አጣሪ ትችት መቃኘቱ ተገቢ ይመስለኛል።

መደበኛ ምሁርነት እና (በትግሉ) የሃሳብ እንቅስቃሴ

“ምሁር” የሚለዉ ቃል ብዙዉን ጊዜ የሚገልጸዉን የተለመደ ጠቅላላ ፍቺ በዚህ ጽሑፍ አገባቦቹ ለመገንዘብ ቃሉን ትንሽ ፈታ አድርጐ ማየቱ ይጠቅማል። በሰፊዉ ወይም ላላ አድርገን ስንወስደዉ ቃሉ የማሰብ ችሎታ ያለዉ የዕዉቀት ሠራተኛ የሚል ትርጉም ይይዛል። እዚህ ላይ በከፍተኛ አካዳሚያዊ ሥልጠናና ማእረግ ሙያተኛ ምሁር መሆንን ወይም መባልን

ከተለያዩ የኑሮም የትግልም ልምዶች፣ ተሰጥዎች፣ ተሞክሮዎችና ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ምሁራዊ ሥራዎች ሠ ሪነ ት ን በአንጻር መለየት እንችላለን።

ሃሳብና ዕዉቀት የተለያዩ ከፍም ዝቅም ያሉ ምንጮች፣ ፈጣሪዎች፣ ደረጃዎች፣ ቅርጾችና ይዘቶች ሊኖሯቸዉ ይችላል። ሁሉም አይነት ዕዉቀት ሙያተኛ ምሁራን በሞኖፖል የሚፈጥሩት ወይም የሚያራምዱት አይደለም። እንዲያዉም በአንዳንድ አገባቦች ምሁራዊ አላዋቂነት ወይም ረቂቅ የዕዉቂያ ልምድ ከተግባራዊ አስተዉሎ ጋር ያለመገናኘት ችግር ሊከሰት ይችላል።

በዚህ መልክ ለዘብ አድርገን ስናየዉ የአይምሮ ሥራ ከባለሙያ ምሁራን ባሻገር በተለያዩ አቀራረቦችና አገባቦች በጋዜጠኞች፣ በአርቲስቶች፣ በኪነ ጥበብ ሰዎች፣ በስነ ጽሑፍ ደራሲዎች፣ በመምህራን እና አልፎ አልፎም በመሕበራዊ ሚዲያ አስተያየት ሰጭዎችና ተቺዎች ከሞላ ጐደል የሚሠራም ነዉ። አንድ ሰዉ መደበኛ የከፈተኛ ትምህርት ሥልጠና የተቀበለ ቢሆንም ባይሆንም ከማወቅ ጉጉት ወይም ከማሰብና ከመራመር አዝማሚያ በመነሳት የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመተርጐምና የመተቸት ልምድ ወይም ተሰጥዎ ያለዉ ከሆነ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ምሁራዊ ሥራ ሠሪ ሊሆን የሚችል ነዉ። በተለያዩ የአገር አድን ትግል መስኮች፣ አቅሞች፣ መንገዶችና አካባቢዎች የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች እንግዲህ ከተለያዩ "ሙያዊ" የሆኑም ያልሆኑም የአይምሮ ሠራተኞች የተቀናበረ አስተዋጽዖ ያስፈልጋቸዋል። ነገር ግን እዚህ ላይ ሦስት ነጥቦች በግልጽ ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ ይታየኛል።

አንደኛ፣ በትግሉ የማሰብ ችሎታና ጀግንነት ወይም ብርታት የግድ ከሙያተኛ ምሁርነት ወይም ከአካዳሚያዊ ማእረግ ጋረ የተያያዘ አይደለም። አንድን ጉዳይ የሆነ ጋዜጠኛ ወይም በከፍተኛ ደረጃ መደበኛ ስልጠናና ማእረግ ያልተቀበለ ግን ራሱን በዕዉቀት ያነጸ ሰዉ በባለሙያነት ምሁር ከሆነ ግለሰብ ይበልጥ ጠለቅ ብሎ ተመርማሪና አሳቢ ሊሆን ይችላል። በትግሉ የላቀ ፖለቲካዊ አድራጊ ፈጣሪነት (political agency) ሊኖረዉም ይችላል።

ስለዚህ በመደበኛ ትምህርት የሚገኙ "ሹመቶች" እሴት የምንሰጣቸዉ ቢሆኑም ወሳኙ ጉዳይ በትግሉ ከፍተኛ አካዳሚያዊ ማእረጐች ያሏቸዉ ምሁራን በብዛት አሉበት ወይስ የሉበትም አይደለም። ዋናዉ ጥያቄ ይልቅስ በትግሉ አስፈላጊና አመራር ሰጪ ምሁራዊ ሥራ ይሠራል ወይ ነዉ። ለዚህ ደግሞ ባለከፍተኛ ዲግሪ ግለሰቦች ጋጋታ አያስፈልግም።

ሁለተኛ፣ በከፍተኛ ትምህርት የተገኘ አካዳሚያዊ ዕዉቀትም ቢሆን ከአገራዊ ንቃተ ህሊና እና ቃል ገቢነት ጋር ለተያያዘ ተጨባጭ ግንዛቤ ወይም አስተዉሎ ዋስትና አይደለም። እንዲያዉም በስሌትም ባይሆን በዉጤት ለተጨባጭ አገራዊ አገባብ ያለዉ የእሳቤና ዕዉቂያ እንቅስቃሴ እንቅፋት ሊሆን ይችላል። በተማሪዉ ንቅናቄ ዘመን ተጀምሮ በአብዮቱ ዘመን ኢትዮጵያ ዉስጥ የተስፋፋዉ ጽንፈኛ የግራ ክንፍ "ምሁራዊ" ገቢር በግልጽ እንዳሳየን "ዕዉቀቱ" አገርንና ህዝብን የማይጠቅም ከመሆን አልፎ ጭራሹን ጐጂ ሊሆን የሚችልም ነዉ።

ሦስተኛ፣ በአገር መታደግ ትግሉ የሙያተኛ ምሁራንን በቂ ተሳትፎ ወይም አልተሳትፎ በሚመለከት በኔ ግምት ዋናዉ ጥያቄ የተማረዉ መደብ አባላት የት ገቡ፣ ከትግሉ ምሀዳር ምነዉ ጠፉ አይደለም። የተማሩ ተሳታፊዎች እጥረት የማይካድ ችግር ቢሆንም በትግሉ ዋናዉ ተግዳሮት ብዙዉን ጊዜ እንደሚባለዉ ዝምብሎ የተማሩ ግለሰቦች ቁጥር ማነስ አይመስለኝም። ከዚህ የተለመደ መነጋገሪያ ጉዳይ ይበልጥ አጠያያቂዉ ነገር በጣም ብዙ ባይሆኑም በተቃዉሞዉ ጐራ በየፊናዉ ላይ ታች የሚሉት ኢትዮጵያዊያን ምሁራን ምነዉ ከድርጅቶች አራቢነታቸዉ ጋር የሚመጣጠን የአስተሳሰብ ታታሪነት ወይም አዲስ የእሳቤ አቅጣጫ አሳይነት ተጓደለባቸዉ ነዉ። ምነዉ በፖለቲካዉ ዓለምና በሃሳቦች መስክ ከመሪነት ይልቅ በአንድ በኩል የሆኑ ያልሆኑ ፓርቲዎችና ወገንተኛ ጐሠኞች ተጐታች ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያን በበጐ አይን በማያዩ የዉጭ ሃይሎችና አገዛዞች (በተለይ በሻብያ) መጠቀሚያና ተጠቃሚ ሆኑ?

የድር ቢያብር አንበሳ ያስርን ምሳሌ በቅጡ ሳይጨብጥ የተማረዉ መደብ በአገር ደረጃ የተባበረ ብርቱ የሃሳብ ንቅናቄ ከመፍጠር ይልቅ ለምን የተከፋፈለ ድርጅቶች "አርብቶ አደር" የርእዮት ፍርክርክነትና ደካማነት ያሳያል? በለዘብተኛነት፣ በጭዋነትና በታጋሽነት ስም ምነዉ ከምሁራዊ ተንቀሳቃሽነት ተገለለ? ለምንድን ነዉ የአገሪቱ የቀለም ሰዎች የአገር

ጉዳዮችንና ችግሮችን ከሥር መሠረታቸዉ ታሳቢ ከማድረግ ወደ ኋላ የሚሉት? ጉዳዮቹ ላይ ሥርዓታዊ ለዉጥ በሚያመጣ መንገድ ሰፋ አድርገዉና ጠለቅ ብለዉ በጋራ የመመራመር፣ የመወያየት፣ የመስማማትና የመንቀሳቀስ ፍላጐታቸዉ ለምን ተዳከመ? በዛሬዉ የለዉጥ ትግል የአገሪቱን ምሁራንን አልተሳትፎ በሚመለከት ዋኖቹ ጥያቄዎች እነዚህ ይመስሉኛል።

የችግሩ አንድ ምንጭ በኢትዮጵያዊያን ዘንድ ምሁርነት የሚተመነዉ ወይም የሚከበረዉ በከፍተኛ ትምህርት ክትትል በተገኙ ማእረጐች ራሳቸዉ መሆኑ ነዉ። እዚህ ላይ ዉስንነታችን መደበኛ ማእረጐቹን ራሳቸዉን ስናጐላና ትልቅ ዋጋ ስንሰጥ በአገር አድን ትግል አገባብ የአስተሳሰብ ለዉጥና መሻሻል የሚያመጣ ወይም ሊያመጣ የሚሞክር ጠበቅ ያለ ምሁራዊ ሥራን ወይም አሳቢነትን ራሱን ግን ተመጣጣኝ ትኩረትና እሴት አንሰጠዉም። ባመዛኙ ለኦፊሴል ማእረጐች ከበሬታ በመስጠት እንወሰናለን።

ማለትም፣ ብዘዉን ጊዜ አንድ ሰዉ ዶክተር ወይም ፕሮፌሰር እገሌ ከተባለ ነገር አለቀ፤ የማወቅ ስሜቱ፣ ንቁ አሳቢነቱ፣ ተንታኝነቱ ወይም ሐያሲነቱ ተረጋገጠ። ያ ሰዉ ምን ያህል ምሁራዊ የማወቅ ጉጉት አለዉ፣ በጥራትና ጥልቀት የአገር ጉዳዮችን ታሳቢ አድርጐስ ያስተዉላል፣ በምን መጠን በሃሳቦች መስክ ከቢጤዎቹ ጋር ይንቀሳቀሳል፣ ወይም ደግሞ ለትግሉ ስልታዊ አቅጣጫ ያሳያል የሚሉ ጥያቄዎች እምብዛም አይነሱም።

በተለያዩ የትምህርትና የሙያ ዘርፎች የሚገኙ አካዲያማዊ ማእረጐች ("ሹመቶች") እንዳልኩት እርግጥ እሴት አላቸዉ፤ አስከባሪ ናቸዉ። ግን በኔ አተያይ ለአገሩ ተቆርቋሪና ታጋይ የሆነ ምሁር እንደ ምሁር ጠቃሚነቱ (አመራሩ) የሚገመተዉ በአርቆ አሳቢነቱ፣ በሐያሲነቱና በስልታዊ ራእዩ ነዉ። በዚህ መንገድ ከቢጤዎቹ ጋር ተባብሮና ተደራጅቶ ንቁ ተሳትፎ ሲያደርግ ያዳበረዉን ጠቅላላ የአስተሳሰብ፣ የትንተናና የአቋም አያያዝ ችሎታ በትግል ሥራ ላይ በማዋል፣ እንዲሁም አማኞችን ብቻ ሳይሆን ተጠራጣሪዎችንም በመሳብ፣ በማግባባትና በማነሳሳት ነዉ።

በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያን ከተያዘችባቸዉ የረጅምና ያጭር ጊዜ ዉጥረቶች ለማዉጣት ዛሬ የሚደረጉ የአገር ወዳድ ወገኖች እንቅስቃሴዎችን ምሁሩ በተጨባጭ ጥናትና ምርምር ከሚገኝ ዕዉቀት ጋር በማገናኘት ብቃቱ መርዳት እንደሚችልና እንደሚገባ እንገነዘባለን። በሃሳቦች መስክ ከአገር ደመኞች ጋር ተፋላሚ በመሆን ሊያግዝ እንደሚችልም እንረዳለን። በዚህ መስክ የተማረዉ አገር አፍቃሪ ሰዉ ጠቃሚነት እጅግ ቢያንስ በሙያተኛ ወይም በመደበኛ የዕዉቂያ ጉጉትና መንፈስ "ተጫዋችነቱ"፣ ማለትም ጥያቄዎችና ሃሳቦች አስተናጋጅነቱ፣ ፈታሽነቱና ተንታኝነቱ ነዉ።

ዳሩ ግን ስንቶቻችን ምሁራን ነን የአገር አድን ትግሉን ለመርዳት በዚህ መደበኛ ደረጃ እንኳን ነፃ ተንቀሳቃሽነት የምናሳየዉ? እኔ ባለፉት አንድ ሁለት አመታት በተሳተፍኩባቸዉ የኢትዮጵያዊያን ምሁራን ዉይይቶች ዉስጥ የተቃዋሚ ፖለቲካ ወገኖችን አስተሳሰብና የትግል አኪያሄድ ከመተቸት እንድቆጠብ፣ ማለትም ሐያሲነቴን ወይም የሃሳብ ጥራት ክትትሌን "በጭዋነት" እንድገድብ፣ በአንዳንድ ባለከፍተኛ ማእረግ "ምሁራን" ተሳታፊዎች ምክር ተሰጥቶኛል።

ምክሩ ሥርዓታዉና ተቺ ሃሳብ የእዉን ፖለቲካ ትግል አጣሪ፣ አልሚና ስልታዊ አቅጣጫ አስያዥ ሊሆን እንደሚችል በቅጡ ካለመገንዘብ አልፎ በድፍኑ የእዉን ትግል አደናቃፊ አድርጐ የሚያይ ይመስል ነበር። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተላለፈዉ መልክት ያሉ "ታጋይ" ድርጅቶችን ተቀላቀል፣ ካልሆነ ደግሞ ትግላቸዉን (በተቺ ሃሳብ/አስተያየት) አታደናቅፍ የሚል ነበር። አዝማሚያዉ የትግል ሃሳቦችን አያያዝና አፈጻጸም ጠጋ ብሎ የማይፈትሽ፣ የአስተሳሰብ ለዉጥን ምንም ያህል እንደ ዋና የሥርዓታዊ ለዉጥ ጉዳይ አድርጐ የማይቆጥር፣ ሆኖ ነዉ የታየኝ።

በተያያዘ ሌላ ሁኔታ ደግሞ ባለፈዉ ሰሞን በኢሳት ያየሁት/ያደመጥኩት ቃለ ምልልስ ትዝ ይለኛል። ትኩረት በሚባል ፕሮግራም በተቃዉሞዉ ጐራ ሃሳቦችን የምናስተናግድበት (የምንሰጥበትና የምንቀበልበት ወይም የምንተችበት) ልምድ ችግር ላይ አስተያየቱን እንዲሰጥ በአሜሪካ የኮሌጅ ፕሮፌሰር የሆነ አንድ ኢትዮጵያዊ ምሁር ተጠይቆ ነበር። ነገር ግን ሆን ብሎም ይሁን አይሁን ፕሮፌሰሩ በጉዳዩ ላይ ምንም አስተያየት ሳይሰጥ ቀርቷል። በጣም እንግዳ የሆነብኝ ነገር ተጠያቂዉ በመምህርነት ሙያዉ የሚያተኩርበት የዕዉቀት መስክ ፍልስፍና ሆኖ ሳለ ሃሳቦች አቀራረባችንና አያያዛችን ላይ ያሉ ችግሮችን በሚመለከት በድግግም ጥያቄዎች ቀርበዉለት አስተያየቱን ሊሰግሰን አለመፈለጉ ወይም አለመቻሉ ነዉ።

እዚህ ላይ ነጥቡ በከፍተኛ ደርጃ የተማሩ ግለሰቦች አሳቢነት ጉድለት ወይም በቂ አለመሆን ሳይሆን (በከፊል ችግሩ ይህ ቢሆንም) በጠቅላላ የአገዛዝም የተቃዉሞም ምሁራዊ-ፖለቲካዊ ልምዳችን የሚያሳየዉ ድክመት ይመስለኛል። ልምዱ በቀጥታና ባንዳፍታ ፖለቲካዊ ወይም ድርጅታዊ አጀንዳ ከመግፋት ባሻገር ብርቱ አገራዊ አነሳስ ያለዉ ሰፋና ጠለቅ ያለ ተቺ ሃሳብ እዉስጡ ማካተት አለመቻሉ ነዉ። ምሁራን እምነታቸዉንና አቋማቸዉን ተከትለዉ የወገንተኛ አጀንዳ አራማጅ መሆን ይችላሉ። ነገር ግን ድርጅታዊ ወይም አገዛዛዊ አጀንዳ አያያዝ አይነት አይነት አለዉ።

ለምሳሌ ገዢዉ የትግሬ ቡድን አሳቢና አዋቂነታቸዉን ገድቦ የጨቋኝ ዘረኛ አገዛዙ መጠቀሚያና ተጠቃሚ ያደረጋቸዉ አማራ ምሁራን ካድሬያዊ አጀንዳ አያያዝ አለ። በዚህ አኳኋን የሚያገለግሉ በከፍተኛ ደረጃ የተማሩ ያገዛዙ “አማካሪዎች” ስለ አገር ጉዳዮች በብቃት የማሰብ ችሎታ ቢኖራቸዉም ከአገዛዙ አጀንዳዎች ዉጪ ዕዉቀታቸዉን ለአገር በሚበጅ መልክ እሥራ ላይ ማዋል የሚያስችል ምን ያህል ሙያዊ ነፃነት ሊኖራቸዉ ይችላል?

የላቀ አይምሮ ወይም የማሰብ ችሎታ ያለዉ ኢትዮጵያዊ ምሁርም ቢሆን በሕወሓት ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ተቀጣሪነት (“አማካሪነት”) ተዳዳሪ እስከሆነ ድረስ ከአገዛዙ ተራ ካድሬዎች ወይም የፕሮፓጋንዳ አቀንቃኞች በመለየት ምሁራዊ ሃቀኝነቱን ጠብቆ መሥራት የሚያስችለዉ የኢኮኖሚ ነፃነትም ሆነ የሙያና የሞራል ጥንካሬ አይኖረዉም። እዚህ ላይ ትኩረታችን የዚህ ወይም የዚያ የተማረ ግለሰብ ዉስንነት (እንበል፣ አድር ባይነት) አይደለም። ይልቅስ ጠቅላላ የአገዛዝ ሥርዓት ምሁራዊ ሙስና እና በተቃዉሞዉ ጐራ ደግሞ ድርጅ የሃሳብ እንቅስቃሴ አለመኖር ነዉ።

የሥርዓታዊ ለዉጥ ኢላማ – የሕወሓት “አብዮታዊ” የአገዛዝ ገቢር

ዛሬም ራሱን የትግራይ ነፃ አዉጪ ብሎ የሚጠራዊ የወያኔ ቡድን ላልተወሰነ ጊዜ ሥልጣን በብቸኝነት ይዞ ለመቆየት የሚንቀሳቀስባቸዉ የተለያዩ መንገዶችና ዘዴዎች አሉት። በዋናነት የታወቀዉ ብልሃቱ ሞገደኛ አገር ከፋፋይና አሰናካይ ዘረኛነቱ ነዉ። ግን ከሌሎች ዘዴዎቹ መካከል ነገደ ብዙ አድር ባዮችን፣ ምሁራንንም ጭምር፣ በመሳብ የአገዛዙ አገልጋዮች ማድረግ፣ ተቃዋሚዎችን በስለላና በስነልቦናዊ ጦርነት ማጥቃት፣ እንዲሁም ከአምባገነናዊ አገዛዙ መረብ ዉጭ ያሉ ድርጅቶች፣ ስብስቦችና የባህል ማህበረሰቦች ዉስጥ ተሸሎክልኮም ሰርጐም በመግባት ከዉስጥም ከዉጭም መጠምዘዝ፣ ማናቆርና ማኮላሸት ይገኙበታል።

የሕወሓት ብቸኛ የሥልጣን አያያዝ ዘዴዎች በተጨማሪ የመንግሥት ንብረትንና በአገር ስም ከዉጭ የሚገኝ እርዳታን በገሃድና በስዉር ጐሣዊ ሙስና ለራሱና ለተጠቃሚዎቹ ሃብት ማካበቻ ማድረግን፣ የሳይበር ቴክኖሎጅ አዉታሮችንና መገናኛ ብዙሃንን የአምባገነናዊ አገዛዙ ተቀጥላና መሣሪያ አድርጐ በመጠቀም የመረጃዎችን ፍሰት ወይም ዝዉዉር እንዳሻዉ መቆጣጠርን፣ እንዲሁም በህዝብ ላይ የሃይል እርምጃ እወስዳለሁ ብሎ መዛትንና በእዉነትም መዉሰድን ያካትታሉ። ገዢዉን ፓርቲ ስንቃወምና ለዉጥ ስንነቃነቅ እንግዲህ እነዚህ የወያኔ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ እዉነታዎች ላይ በማተኮር፣ ባመዛኙ የአገዛዙን ተጨባጭ ጭቆና በማጉላት፣ ፓርቲዉ ያለዉ የ ሃሳቦች እና የ መርሆች አያያዝ ወይም አቀራረብ ምን ጉዳያችን ነዉ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል። ተቃዋሚ ሃይሎች የወያኔ አገዛዝ ላይ የተለያዩ ቀጥታ እርምጃዎች በመዉሰድና በበርካታ የኢኮኖሚ፣ የህብረተሰብና የባህል ዘርፎች የተቀናበሩ አማጺ እንቅስቃሴዎች በማድረግ ገዢዉ ቡድን ከሥልጣን እንዲለቅ፣ ካልሆነም ለእዉነተኛ ድርድር እንዲቀርብ “የሚያበረታታ” እና የሚገፋፋ ቀጣይ ተጽእኖ ለምን አያሳርፉበትም?
በሌላ አነጋገር፣ የሕወሓትን “ገዢ” ርእዮት እና የፖለቲካ አመክንዮ ወይም አመኔታ ችላ ብሎ ተጨባጭ ፖሊሲዎቹንና ድርጊቶቹን ፊት ለፊት መቃወም ይበልጥ ዉጤታማ አይሆንም ወይ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል። የሕወሓት አገዛዝ ከፕሮፓጋንዳ እንቅስቃሴዎች ዉጭ በፖለቲካ መርሆች ሜዳ በመሰሪነት ሳይሆን በበጐ እምነት ተወዳዳሪ ስላልሆነ፣ በሜዳዉ ስለሌለ፣ አገዛዙን ለምንስ በሃሳቦች ዉጊያ መግጠም ያስፈልጋል? ከራሱ ጠባብ ወገንተኛ ጥምዘዛና አተረጓጐም ዉጪ ለመሠረታዊ ፖለቲካ እሳቤ ምንም ያህል ዋጋ ወይም ክብደት ከማይሰጥ ገዢ ፓርቲ ጋር ተቃዋሚ ሃይሎች የአስተሳሰብ ፉክክር ማድረግ ለምን ግድ ይላቸዋል?

ቀጥታ የተቃዉሞ እንቅስቃሴዎች በርግጥ በአገር አድን ትግሉ ዉስጥ ተገቢ ቦታና ሚና አላቸዉ፣ በተለይ በትግሉ ያጭርና

የመካከለኛ ጊዜ ሂደት። ይሁን እንጅ እንቅስቃሴውቹ በራሳቸዉ ወይም እንዳሉ ኢትዮጵያን ከምትገኝበት ለአስርተ አመታት ከተጠራቀመ የረጅም ጊዜ የአብዮታዊነት ልምድና አገዛዝ ዉጥረት ከማዉጣት አኳያ በቂ አይሆኑም።

በተወሰነ ዘር ተኮር አገባብም ቢሆን ልምዱ የፖለቲካ ስነአመክንዮ ወይም አስተሳሰብ ቅርጽና ይዘት አለዉ። ይህን ልምድ ሕወሓት ከሌሎች የማንነት ፖለቲካ አድራጊ ፈጣሪ ሆነዉ በአገሪቱ ምድር ከተንቀሳቀሱና ዛሬም ከሚንቀሳቀሱ ወገኖች ጋር በመሠረቱ ይጋራል።

እንደ አገር ዛሬ ለሥር ነቀል ለዉጥ ኢላማ ማድረግ ያለብን እንግዲህ በተለይ የአንድ የተወሰነ ፓርቲ "አብዮታዊ" አገዛዝ ብቻ አይደለም። በጠቅላላ የምናነጣጥረዉ በተደራጁ ርዕዮታዊ እንቅስቃሴዎች አማካኝነት የተጸነሰና የታነፀ፣ ፓርቲም ጐሣም ዘለል የሆነ፣ ተራማጅ ተብዬ አምባገነናዊ የአስተሳሰብና የገቢር ፓራዳይም ወይም ሥርዓት ጭምር ነዉ።

የወያኔ ትግሬዎች ጥሬ ዘረኝነትም ሆነ እንደ ፖለቲካ ዕቅድ የሚከታተሉት ብሔርተኛ

ጐሠኝነት ( nationalistic ethnicism) የዚሁ "አብዮታዊ" ሥርዓት ፈጠራ ነዉ። እዚህ ላይ እግረ መንገዴን አንድ ነገር ግልጽ ላድርግ። በጽንሰሃሳብ ደረጃ ብሔርተኛ ጐሠኝነት ስል ብሔራዊ ነፃነት ( national liberation ) የሚለዉ ሃረግ በአብዮተኞቻችን ከተሰጠዉ ድብስብስ ትርጉም ለይቼ ነዉ።

ማለትም፣ በኢትዮጵያ፣ በተለይ በትግራይና በኦሮሞ አካባቢዎች አገባቡ የኋለኛዉ ጽንሰሃሳብ በታሪክ ወይም በባህል ቀድሞ የተሰጠ ወይም የነበረ አገር (ብሔር/nation) ነፃ የመዉጣት ጉዳይ ሳይሆን ያልነበረና የሌለ አገራዊነትን ወይም ብሔራዊ ማንነትን ራሱን መፍጠር አላማዉ ካደረገ ወገንተኛ የጐሣ ብሔርተኝነት እቅድ ጋር የተያያዘ ምኞት ወይም ሃሳብ ነዉ። ለምሳሌ ነፃ ሊወጣ የሚችል የኤርትራም ሆነ የትግሬ ብሔራዊ ወይም አገራዊ ማንነት (ራስነት) በታሪክ ኖሮ አያዉቅም። በሁለቱም ምሳሌዎች በተመሳሳይ መንገድ ያየነዉ ብሔራዊ ማንነት ራሱ ባመዛኙ የአንድ ብቸኛ፣ አምባገነናዊ ፓርቲ የፖለቲካ ፈጠራ እንደሆነ ነዉ።

እንግዲህ በርግጥ መሠረታዊ የሥርዓት ለዉጥ ከፈለግን አንድ ሁለት አማካኝ ጥያቄዎች ማንሳት (ብሎም መመለስ) ግድ ይላል። የኸዉም በቀጥታና ባንዳፍታ የምናያቸዉን ያፈጠጡ ያገጠጡ የወያኔ አገዛዝ አገር ጉጂ ፖሊሲዎችን ወይም ድርጊቶችን የሚያወግዙና ዉድቅ የሚያደርጉ ክርክሮች/ተቃዉሞዎች ከማቅረብ ባሻገር ምን አይነት የአገር አድን ትግል መንገድ መያዝ ይቻላል?

በሌላ አነጋገር፣ ድርጅቶች በማራባት በየፊናዉ በታክቲካዊ ተቃዉሞ ከመንቀሳቀስ በተረፈ ምን ማድርግ ያስፈልጋል? እስከ መቼ ነዉ ከጠቅላላ ስልታዊ ራዕይና ሃሳብ ጋር የማይገናኙ ቅርጽ የለሽ "ተግባራዊ" የተቃዉሞ መልሶች በመስጠት ብቻ ተጠምደን ልንቀጥል የምንችለዉ? በዚህ የተወሰነ ደረጃ የምንወስዳቸዉ የተለመዱ ወይም የለት እለት እርምጃዎች ዘላቂ መዋቅርና አቅጣጫ መሰጠት የሚያስፈልጋቸዉ አይደሉም ወይ በኔ ግምት ኢትዮጵያ አገራችንን ከገጠማት ዉስብስብ ዉጥረት ለዘለቄታዉ የማዉጣት ንቅናቄ ገዢዉን ፓርቲ በመወንጀልና ዉድቅ በማድረግ ወይም ከፓርቲዉ ጋር በተነጣጠሉ የትግል መስኮች ወይም አካባቢዎች ዙሪያ የእዉን ተኩስ በመለዋወጥም ሆነ የ ፖለሚክ እና የ ፕሮፓጋንዳ እሩምታ በመስጣጠት የሚወሰን አደለም። ይህ መንገድ የሥርዓት ለዉጡን እቅድ፣ ብሎም የአገር ነፃ ማዉጣቱንና መልሶ ማጠናከሩን ትግል ሩቅ አይወስደዉም። መንገዱ እንዲያዉም ትግሉን ከመሬት አስነሺ፣ ማለትም አንደርዳሪና መንጣቂ ኃይል ማግኘት ያስችለዋል ማለት አንችልም ከዋለ ካደረ፣ "አብዮታዊ" አገዛዝ ተሻጋሪ ከሆነ ጨቋኝ መዋቅር ወደ ተሻለ ሃቀኛ፣ ፍትሐዊና ዲሞክራሲያዊ መንግሥት እንደ አገር መሸጋገር ከፈለግን "ተራማጅ" ስንለዉ የኖርነዉና ዛሬም ከሞላ ጐደል ያልተለየንን አምባገነናዊ የፖለቲካ ባህል ጥልቅ ብልሹነት በግልጽ ማስቀመጥና አማራጩን መተለም አስፈላጊ ነዉ። ይህን ለማድረግ ደግሞ ጠበቅ ያለ ምሁራዊ እንቅስቃሴ የሚጠይቅ መሠረታዊ የፖለቲካ አስተሳሰብና ገቢር ለዉጥ ማድረግ ግድ ይላል። በዚህ መሠረታዊ የለዉጥ ትግል ዉስጥ ወሳኙ የመጀመሪያ እርምጃ የለዉጡን ኢላማ በሥርዓታዊ ገጽታዉና ይዘቱ ግልጽ ማድረግ ነዉ። ዋናዉ ተለዋጭ ነገር አብዮታዊ ነኝ ባዩ ሕወሓት የኢትዮጵያ መንግሥት፣ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ህብረተሰብ ላይ ወገንተኛ ኃይሉን ለመጫን የተጠቀመበት ሁለ ገብ የአገዛዝ ዉጥን (hegemonic project) ነዉ።

የተለያዩ ክፍሎች ያሉት ይህ የጐሣ ፖለቲካን ያማከለ የአገዛዝ እቅድ አናሳዉን የወያኔን ፓርቲ ለሩብ ምእተ አመት የታላቋ ኢትዮጵያ ብቸኛ ገዢ ለመሆን አብቅቶታል። የዕቅዱ ክንዉን ገዢዉን ጠባብ የጐሣ ፓርቲ በሃሳቦች ሜዳ፣ በከፍተኛ ትምህርት ረድፍ፣ በመንፈሳዊ ኑሮ ዘርፍ፣ በኢኮኖሚ ልማት እንቅስቃሴዎች ዙሪያ፣ በአገር ጦር ሃይሎች አወቃቀርና አመራር፣ እንዲሁም በባህላዊና ነገዳዊ ማህበረሰቦች ማንነቶች ሰርጐም ተሽሎክልኮም ገብቶ በወገንተኛነትና ዘረኛነት ሁሉን ነገር አድራጊ ፈጣሪ መሆን አስችሎታል።

ሕወሓት በዚህ መንገድ በኢትዮጵያ የተለያዩ የህብረተሰብ፣ የባህል፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዘርፎች በቅንብር የሚንቀሳቀስ ሄጅ መ ናዊ ሃይል እንደሆነ እንረዳለን ማለት ነዉ፣ ሄጅመናዊነቱ በጣም ዉስን መሆኑን ሳንዘነጋ። በዚህ ኩነቱ ነዉ ፓርቲዉ በግልቡና በጠባቡ ዘረኛ ቡድን ቢሆንም የአገዛዝ መረቡን በኢትዮጵያ አስፋፍቶ ለመዘርጋት የበቃዉ። የወያኔ ገዢ ቡድን ጭቆና በአገር ነፃ አዉጪ ወገኖች ዋና የመሠረታዊ ለዉጥ ኢላማ ሲሆን እንግዲህ በተለያዩ ተናጠል አላማዎቹ፣ ፖሊሲዎቹና ድርጊቶቹ፣ አለዚያም በነገዳዊ ማንነቱ ወይም በጥሬ ዘረኝነቱ አይደለም።

ይልቅስ በሁለ ገብነት እነዚህን ሁሉ አጠቃለዉ ባካተቱ ቅንብር ሄጅ መ ናዊ ገቢሮቹ ነዉ የሥርዓታዊ ለዉጥ ኢላማ የሚሆነዉ። አገዛዙ ሁለ ገብ ነዉ የምለዉ በራስ ጠቀምነት አለገደብ ከሚገባባቸዉ በርካታ የመንግሥት፣ የኢኮኖሚ፣ የህብረተሰብና የባህል ዘርፎች አኳያ ብቻ አይደለም። በተጨማሪ እንደ አገዛዝ ራሱ የሚንቀሳቀስባቸዉን አምባገነናዊ ሃሳቦች፣ ግቦች፣ እቅዶችና አኪያሄዶችም እግምት ዉስጥ በማስገባት ነዉ።

እነዚህ ገደብ የለሽ እንቅስቃሴዎቹ ለድርድር ቀርቶ ትርጉም ላላቸዉ ምክንያታዊ የምሁራንም ሆነ የፖለቲካ ወገኖች ዉይይቶች ክፍት ያልሆኑ "አብዮታዊ" እና "ልማታዊ" የተባሉ ግግር የእሳቤ ፎርሙላዎች በአንድ ጐን (unilaterally) ሥራ ላይ ማዋልን፣ በኦፊሴል ወይም በግልጽና በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ ብቸኛ የትግሬ ብሔርተኝነት ("የታላቋ ትግራይን" እቅድ) ማለምን፣ ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ አማራ የባዕድ ቅኝ አገዛዝ መንፈስ ማንጸባረቅን፣ በተሰላ ፖሊሲም ሆነ በዉጤት ጐሣ ተኮር አገዛዛዊ ሙስና ማስፋፋትን፣ በሰላማዊ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎችና በንጹህ ዜጐች ላይ ግልጽም ድብቅም የሃይል ጭቆና እርምጃዎች መዉሰድን ያካትታሉ።

ሆኖም እዚህና በተከታይ ጽሁፍ እኔ ትንሽ ጠጋ ብዬ የማየዉ የወያኔ ፓርቲ በተለይ በፖለቲካ ሃሳቦች መስክ የሚገኝበትን የተወሰነ ሄጅመናዊ የአገዛዝ ሁኔታ ነዉ። እንደሚመስለኝ የሕወሓትን ሁለ ገብ ጨቋኝ አገዛዝ ከሥር መሠረቱ ለመቋቋም ብቻ ሳይሆን የሚተካዉን አማራጭ ሥርዓት በመርህም በስልትም ለመገንባት አገር ወዳድ ወገኖች በፖለቲካ ሃሳቦች መስክ ጠለቅ ብለዉ ገብተዉ መንቀሳቀሳቸዉ ወሳኝ ነገር ነዉ።

በዚህ አይነት አኪያሄድ ዘረኛዉ አገዛዝ ብርቱ የአገርና የህዝብ ጉዳዮችን በብቸኝነት ና በአምባገነንነት የቀረጸበትን የተወሰነ " አብዮታዊ " የፖለቲካ ቋንቋና ባህል ከጉዳዮቹ ራሳቸዉ መለየት አስፈላጊ ነዉ። ጉዳዮቹ እንዳሉ ለአማራጭ አቀራረጾች ክፍት ናቸዉ። አንድ ወገንተኛ ድርጅት ወይም አገዛዝ ላንዴም ለሁሌም የተሟላ ምንነትና ቅርጽም ሆነ ትርጉም ሊሰጣቸዉ ከቶ አይችልም። ዘረኛ ሆነም አልሆነም ወገንተኝነት ወይም የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ከሙሉ አገራዊነት ቀርቶ ከነገዳዊ ማህበረሰብ ማንነት ወይም ራስነት ጋር እኩል ተደርጐ የሚታይ አደለም።

የወያኔን ጐሡኛ ፖለቲካ የሚደግፉ በርካታ ትግሬዎችና ትግሬ ያልሆኑ የአገዛዙ ተጠቃሚና መጠቀሚያ ኢትዮጵያዊያን ቢኖሩም አምባገነናዊዉ ሕወሓት ኢትዮጵያን ቀርቶ የትግራይን ህዝብ አይወክልም። ገዢዉን ፓርቲ ወደደም አልወደደም፣ ደገፈም አልደገፈም የትግራይ ህዝብ በፈላጭ ቆራጩ ወያኔ ፓርቲ የተያዘ ነዉ፤ በፓርቲዉ ጥብቅ ቁጥጥር ሥር ያለ ነዉ። ኢትዮጵያ ራሷ ሕወሓት በተጻራሪነትና በደመኛነት መንፈስ የያዛት "ምርኮኛ" አገር (captive nation) ናት። ነፃ መዉጣት ትፈልጋለች፣ ትጠብቃለችም። አማራዉ በተለይ ደግሞ ወያኔ ትግሬዎች በይፋ በጠላትነት የፈረጁት ህዝብ ነዉ። ስለዚህ የሕወሓት አገዛዝ እንደ አገዛዝ የሚናገረዉን "ብሔሮች" እና "ህዝቦች" የሚል ራስ ጠቀም ግን ፀረ አንድነት የፖለቲካ ቋንቋም ሆነ ከቋንቋዉ ጀርባ ያለ በብቸኝነት ወገንተኛ የሆነ ስታልናዊ አስተሳሰብ ከአገሪቱ ማህበረሰቦች ተደራራቢና ተወራራሽ የባህል ማንነቶች ወይም አገራዊም አካባቢያዊም ራስን በራስ አተያዮች ጋር መደባለቅ የለብንም።

ጠባብ ዘረኛ ወገንተኝነትን ከሙሉ ነገድነትም ሆነ ብሔርነት/አገርነት በግልጽ መለየት ያስፈልጋል። ይህ ልዩነት በጣም ብርቱ ጉዳይ ነዉ። የወያኔ አገዛዝ የተቋቋመዉና ቀጣይነት ያገኘዉ ይህንኑ መሠረታዊ ለዩነት (ማለትም፣ በአንድ በኩል የራሱን ወገንተኛ ዘረኝነት በሌላ በኩል ደግሞ የምህበረሰቦችን ጥቅል ነገዳዊነት - አገራዊ ነት ) ሆን ብሎም ይሁን ሳያዉቅ በማምታታት እንደሆነ ምንም ያህል ስዉር አይደለም።

ይህን በመረዳት ሕወሓት እንደ አገዛዝ የሚንቀሳቀስበትን "አብዮታዊ" የአስተሳሰብና የአነጋገር ገቢር ወይም ተለምዶ ለይቶ የሥርዓታዊ ለዉጥ ኢላማ ማድረግ ይቻላል፤ ያስፈልጋልም። ተለምዶዉ የሥርዓታዊ ለዉጥ ትግል የሚነጣጠርበት እንዳልኩት ከገዢዉ ፓርቲ ጋር ብቻ ባለዉ ትስስር አይደለም። ሌሎች ነባር አበዮተኛ ወይም "ተራማጅ" ወገኖችና ፓርቲዎች ለየቅልም ሆነ በወል በአገሪቱ ካስፋፉት በጥልቅ እንከናማ ከሆነ የፖለቲካ አስተሳሰብ ባህል ጋር ባለዉ ቅርብ ግንኙነትም ነዉ።

ለምሳሌ ኢሕአፓ፣ ሕወሓትና ኦነግ በተወሰነ ደረጃ የወገንተኝነት ልዩነቶችም ጠቦችም የነበሯቸዉና ያሏቸዉ ቢሆንም "የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል" በሚል ግዑዝ ስታሊናዊ ቋንቋ የተቃኘ ፎርሙላዊ "ተራማጅነት" ወይም "ፖለቲካዊ ትክክለኛነት" በመሠረቱ ተጋርተዋል። ስለዚህ የዛሬዉ የለዉጥ ትግል አይነታ ኢላማ የዚህ ወይም የዚያ ፓርቲ አገር አሰናካይ ብቸኛ ወገንተኝነት/ገዢነት አይደለም። ይልቅስ የሥርዓታዊ ለዉጡ ዋናዉ ማነጣጠሪያ የተለያዩ አብዮተኛ ፓርቲዎችና ዘዉጌ ድርጅቶች ከሞላ ጐደል የተጋሩት በስሌትም ሆነ በዉጤት አገር ከፋፋይ የዘር ፖለቲካ የሚያራምድ ነባር "አብዮታዊ" ልምድ ነዉ።

ይህ ሄጅመናዊ ገቢር ምን ይመስላል፣ በተለይ በሕወሓት አገዛዛዊ ገጽታዉ? በዉስጡ የሃሳቦች ቦታ ወይም ሚና ምንድን ነዉ፣ ሥራ ላይ የሚዉሉትስ እንዴት ነዉ? ለነዚህ መሠረታዊ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ መስጠት ለሥርዓታዊ ለዉጡና ለአማራጩ ግንባታ ንቅናቄ ወሳኝ የመጀመሪያ እርምጃ እንደሆነ እገነዘባለሁ።

እዚህ ገቢር የሚለዉን ቃል የምጠቀምበት ከረቂቅ ሃልዮ (theory) ወይም ከሃሳብ በተለየ ፍቺ ሳይሆን በሃሳቦችና እምነቶች መስከም ተጽዕኖ አሳራፊነቱን እግምት ዉስጥ ባስገባ ትርጉም ነዉ። በዚህ ትርጉሙ ገቢር (ሰፋ ባለ የእንግሊዝኛ ፍቺዉ practice) ከ ባህል ወይም ከ ልምድ ጋር በመጠኑ ተመሳሳይ ነዉ። እዚ ላይ ዋናዉ ነጥብ ረቂቅ ሃሳቦች (ለምሳሌ "ህገ መንግሥት"፣ "ዲሞክራሲ"፣ "የብሔር ማንነት") ሕወሓት በበላይነት ከሚቆጣጠረዉ ሁለ ገብ "አብዮታዊ" ሥርዓት ወይም ፓራዳይም ባሻገር፣ ማለትም ከገዢዉ ቡድን ብቸኛና አምባገነናዊ የአቀራረጽ፣ ያተረጓጐምና ያፈጻጸም ልምድ ወይም መስተዳደር ዉጪ፣ ምንም ሕይወት የላቸዉም። እንዲኖራቸዉም ሕወሓት አይፈልግም።

ከአማጽያን እንቅስቃሴዎች ባሻገር በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ አሳቢነት ወይም አድራጊ ፈጣሪነት ራሱ የወያኔ "አብዮታዊ" ፖለቲካና አገዛዝ ገቢር ተስፋፍቶ የሚገለጥበት ወይም የአገዛዙ ተጽዕኖ ተሸሎክልኮ የሚገባበት መስክ ነዉ። ገዢዉ ወገን እንደፈለገዉ የሚጠመዝዘዉ ሁለ ገብ የእንቅስቃሴ ልምድ እንግዲህ ከሃሳቦችና ማንነቶች ቀደምትነት ያለዉ ነዉ። ይህም ማለት በገዢዉ ቡድን ቁጥጥር ሥር ሃሳቦች፣ እንበል "ህገ መንግሥት" እና የጐሣ "ማንነት"፣ እንዴት እንደሚሠሩ ወይም እንደማይሠሩ ተገቢ ግንዛቤ ለማግኘት ከጅርባቸዉ ያለዉን የቁጥጥር፣ ማለትም ተጨባጭ ያቀራረጽና ያፈጻጸም ልምዶች ጠለቅ ብሎ መፈተሽ፣ ብሎም ማፈራረስ ግድ ይላል።

የዚህ አይነት ባንዴ አፍራሽም ገንቢም የሆነ የአማራጭ ሥርዓት ፈጠራ መንገድ የሚጠርግ የተቃዉሞ እንቅስቃሴ ሲደረግ የሚነሳዉ ጥያቄ ምንድን ነዉ? በኔ ግምት የወያኔ አገዛዝ ሃሳቦችን፣ ፖለቲካንና የኢትዮጵያን ነገዳዊ ወይም አካባባዊ ማህበረሰቦችን ማንነቶች በበላይነት ይቆጣጠራል ወይ የሚል ጥያቄ አለመሆኑ ግልጽ ይመስለኛል። ጉዳዩ ወያኔ ለምን የተወሰነ የእሳቤ ቁጥጥር ያደርጋልም አይደለም። አገርንና ህዝብን ጠቀመም ጐዳም ማንኛዉም ገዢ ፓርቲ ወይም የህብረተሰብ መደብ ራስ ጠቀም የሃሳቦችና መርሆች መስተዳደር ( governance ) ማድረጉ አይቀሬ ነዉ፣ ራስ ጠቀምነት በተለያየ መልክና መጠን የሚገለጽ ቢሆንም።

ይልቅስ ዋናዉ ጥያቄ ሕወሓት እንዴት ነዉ በተወሰኑ አብዮታዊ የተባሉ ቅንብር ገቢሮቹ አማካኝነት ሃሳቦችንና የጐሣ ማንነቶችን ብቸኛ ቅርጽና ይዘት በመስጠት የሁለ ገብ አምባገነናዊ አገዛዙ ተቀጥላና መሣሪያ ማድረግ የቻለዉ፣ እንዴትስ ነዉ ይህን የገቢሮች አዉታር በአገራዊ ተቃዉሞ መፈታታት የሚቻለዉ የሚል ይሆናል። እንደ አገር ጠባችን በጠቅላላ ከእሳቤ አስተዳደር ጋር ሳይሆን ከተወሰነ አበዮታዊ የተባለ ፀረ አንድነት የአስተሳሰብ ቁጥጥር ገቢር ወይም ልምድ ጋር ነዉ። ድርጁ ትስስር ያላቸዉ የተለያዩ የወያኔ አገዛዛዊ ገቢሮች ለአንድ አላማ አንድ ወጥ የእንቅስቃሴ ሥርዓት የፈጠሩና አገር ከፋፋይ አገዛዙን ላልተወሰነ ጊዜ ቀጣይ ለማድረግ የታቀዱ ናቸዉ። በዚህ ሥርዓት ወይም መረብ አማካኝነት ገዢዉ ቡድን ሲንቀሳቀስ በጠባብነትና ብቸኝነትም ቢሆን ድርጅታዊ ቋሚነት ወይም ድንበኛነት፣ የአስተሳሰብና ያሠራር ቅንብር፣ እንዲሁም አፈ ቀላጤነት ወይም የቃል በቃል (ፖለቲካዊ) ንግግር ቅልጥፍና አለዉ። በተለይና በብቸኝነት የራሱ የሆኑ አመለካከቶች ብቻ ሳይሆኑ የራሱ “ሃቆች” እና “እዉነታዎች” አሉት። በጠቅላላ ገዢዉ የወያኔ ቡድን የሚንቀሳቀሰዉ ከኢትዮጵያዊነት ጋር ብቻ ሳይሆን ከነገዳዊና አካባቢያዊ ማህበረሰቦች አንጻራዊ ነፃነትም ሆነ አገራዊ ትስስር ጋር ከማይገናኝ የቡድኑ ራሱ አጓዳኝ “ብሔራዊ” አለም (parallel “national” universe) ዉስጥ ነዉ ማለት እንችላለን። በዚህ አኳኋኑ ሃሳቦች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፍ የሚችለዉ በቀጥታ የፖለቲካ ሃይልና ፕሮፓጋንዳ በመጠቀም እንጂ የአገር ጉዳዮችን በቅጡ ታሳቢ በሚያደርግ ነፃ ምክንያታዊ ክርክርና የሃሳቦች ልዉዉጥ አይደለም። ወይም ደግሞ በሰፊዉ የኢትዮጵያን ህዝብ አግባቢ የሆነ ምሁራዊና ሞራላዊ አመራር በመስጠት አይደለም። የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በዚህ መልክ የኢትዮጵያን ምሁራንና ህዝብ አግባቢ መሪ ለመሆን ፈቃደኛነቱም ሆነ ችሎታዉ የለዉም።

ይሁን እንጂ አገዛዙ ፖለቲካዊ ስነአመክንዮ ወይም ባህል አካቶ የለዉም ማለት ልክ አይደለም። በጥልቅ እንከናማ በሆነ “አብዮታዊ” ገቢር የረቀቀም ቢሆን፣ ገዢዉ ፓርቲ በሃቀኝነት ይመንበትም አይመንበትም፣ የወያኔ አገዛዝ ሄጅመናዊ ሊሆን የበቃበት በማንነት ፖለቲካ ዙርያ የተዋቀረ ርእዮታለማዊ አዉታር ወይም የሃሳብ ይዘታ አለዉ። አገዛዙ እርግጥ በዋናነት ጥሬ ጉሠኝነትን ያካትታል፤ ሆኖም የማንነት ፖለቲካ ገቢሮቹ በጥሬ ጉሠኝነት የተወሰኑ አይደሉም። በተከታይ ጽሑፍ (ክፍል ሁለት) ሃሳቦች፣ እንዲሁም የዘር ማንነት ህንፀቶች፣ በአገዛዙ ሥር ያላቸዉ ቦታና ዝዉዉር ላይ የተማከለ ተቺ ትንተና አቀርባለሁ። አያይዤም አገር አድን ትግሉ “ገዢዎቹን” ሃሳቦች እንዳኳኋናቸዉ እንዴት ሊቋቋማቸዉና የአስተሳሰብ ለዉጥ ሊያደርግ እንደሚችል ለማሳየት እሞክራለሁ

ጸሐፊዉን በኢሜል ለማግኘት፣ tdemmellash@comcast.net